# <u>የወያኔዎች ያቀዱት የትግራይ የግንጣላ አጀንዳ ውጭ አገር በሚኖሩ በአንዳንድ ታዋቂ ወጣት አማራዎች ይሁንታ እያገኘ ነው</u>

## ***ጥያቄ ለወጣት ሔኖክ የሺጥላ***

<u>ጌታቸው ረዳ (ኢትዮ ሰማይ አዘጋጅ)</u>

ወያኔዎች ያቀዱትን ኢትዮጵያን የማፈራረስ አላማ በቁጣ የከተቱት ውጭ አገር የሚኖሩ አንዳንድ ኢትዮጵያዊያን ወጣት አማራዎች ወደ ወጥመዳቸው ሰተት ብሎ እየገባላቸው መሆኑን ሰሞንን ከታዘብኩት ሁኔታ እንነጋገርበታለን።

ከ1966 ዓ.ም ጀምሮ አሁን ላለንበት ውጥንቅጥ ጨለማ የከተቱን ቀንደኛ ተጠያቂዎች፤(ጣልያኖች እና እነ ሮማን ፕሮቻስካን ዓረቦች... እንዳለ አስቀምጠን) አገር ውስጥ በቀል “አፍራሽ ሃይሎች” የሆኑት የግንጠላ ፍልስፍና ሰባኪዎች፤ የያኔ ተማሪዎች የነበሩ ሃይማኖተ ቢስ ወዛደር ላብ አደር ገበሬ ሃብታም ድሃ እያሉ “በየመደቡ/ እንደዛሬው ብሄር፤ብሔረሰብ/ክልል መድበው” ሕዝብ እርስ በርሱ እንዲጋደል እና እንዲጣላ ያስተላለቁ የኮሚኒስት አስተዳዳር አቀንቃኞች የነበሩት ኢሕአፓዎች፤መኢሶኖች/ደርጎች/፤አነጎች እና ወያኔዎች... መሆናቸው ላሰምርበት እወዳለሁ። ከሥረ መሠረቱ የዚህ ብጠብጥ ርዕዮት መነሻ እና መድረሻ ካልተረዳን ትግላችን ከማን ጋር እንደሆነ አላወቅንምና የብጥብጣችን አካሎች የሆኑት ከላይ የተጠቀሱ የፋሺስት ኮሚኒዝም አምባገነንነት ያቀነቀኑትን “አጀንዳ’ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መልሰን ድሮ ያቀነቀኑትን አጀንዳ መድገማችን አይቀሬ ነው። ውጭ አገር ያለው የዛሬው ወጣት በንህሊሰት <u>አፍራሽ ስሜት</u> ተወጥሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግዛቶች/ነገዶች “በተለይ” <<የኢትዮጵያ ሕዝብ አካልና የኢትዮጵያ ግዛት የሆነው ትግራይን ሕዝብ ቢገነጠል ደንታ እንደማይሰጣቸው>> ሕዝብን እያብጠለጠሉ የትግራይ ሕዝብ ድንጋያማ መሬት የተፈጠረ “እባብ እያየ ያደገ ልጅ ” (ትግሬዎች ዓፋሮች፤ሸዋዎች፤ሶማሌዎች..) እና “ሙዝ እና ብርቱካን እያየ ያደገ” “ምናልባትም አማራው ለማለት ይመስላል’ እና የተቀሩት ይመስለኛል፤ (ምክንያቱም ሶማሌ እና ዐፋር መሬት ያለው ሕዝባችን በስማቸው ባይጠቅስም የሚኖሮው ድንጋያማ እና ምድረበዳማ አካባቢ ስለሆነ እነሱም ከኛው ከትግሬዎች እኩል “እባብ እያዩ” ያደጉ ናቸው እየተባልን በወጣት ሔኖክ የሺጥላ አዲስ የማሕበረሰብ የባሕሪ ምደባ ፍልስፍና አዲስ ትንተና ማድመጥ ጀምረናል። (ቪዲዮውን እዚህ ለማየየዝ

ፈልጌ አድራሻውን ስላጣሁት ምናልባትም ሌሎቻችሁ ፈልጋችሁ ብታገኙት ሞክሩት)።

ቁጣዎቻችን መቆጣጠር ካልቻልን ፤በተለይ ወጣቶች የሆናችሁ፤ አብሶ ደግሞ ከእሳቱ ጦስ በብዙ ሺሕ ኪሎሜትር ርቃችሁ በሌላ ዓለም የምትኖሩ ወጣት ኢትዮጵያዉያንም ሆነ ማንም ፍጡር ስሜት እንዳይቆጣጠራችህ ብርቱ የራስ ትግል ካላደረጋችሁ፤ ከኛ ርቀው በሚገኘው ሕዝባችን ላይ እሳት እየጫራችሁ አገሪቱ እንድትበታተን የሚፈልጉ ወያኔዎች፤አነጎች እና ኦጋዴኖችን አጀንዳቸው በማቃለል አላስፈላጊ ስሜቶችን በመከናነብ ሕዝብ ላይ ጸያፍ ዘለፋ በመወርወር ሕዝብን በማስቆጣት ተጨማሪ /ጭራሮ/ እንጨት/ በማቀበል እሳት ቆስቋሾች ላለመሆን እና ወጥምዳቸው ውስጥ ላለመግባት ጥንቃቄ ካላደረጋችሁ አገራችሁ በማትወጣው ወጥመድ ውስጥ ልትገቧት ነው። ይህ ሃቅ ላለመቀበል እና ስሜቶችን ላለመቆጣጠር የተፈለገው የመከላከያ ምክንያት ቢቀርብም፤ ውጤቱ ግን የመጀመሪያ ተጠቂዎች እዛው አገር ውስጥ ያሉት ተራ ምስኪን ሕዝብ መሆኑን ልገልጽ አወዳለሁ።

ወጣት ሔኖክ የሺ ጥላ በቅርቡ ደጋግሞ የሚናገራቸው ስለ ትግራይ ሕዝብ አልጣሙኝም። የሚናገረው ገብቶት (ሆን ብሎ) ይሁን ባለማወቅ/በቁጣ ስሜት/ ተገፋፍቶ (ለማብራራት ቢቸግርም) አንድ እጅግ ሳከብረው የነበረ ወጣት ይናገረዋል ብየ ያልጠበቅኩትን "የትግራይን ሕዝብ በድህነት መሬት መፈጠሩን (የትግራይ መሬት ታሪክ እየገለጸው ላለው ምክንያት ለምን እንደሆነ ያወቀው አይመስለኝም) እያናናቀ (ትራምፕ የተባለ ንዮ-ፋሺስት የአሜሪካ ፕረዚዳንት *"ከ ሺት ሆል"* የተፈጠሩ ሲል ሦስት የጥቁር ሕዝብ አገሮችን በንቀት ሲኩራራ በዓለም እና አፍሪካኖች ፊት ለውግዘት እንደተጋረጠ ሁሉ፤ ይህ ስለ አማራ ቆሜአለሁ የሚለን ወጣት ሔኖክ የሺጥላ (እባካችሁ ስለ አማራ ደህንነት ቆመናል የሚሉትን ስለ አገሪቱ አንድነት እና ሕዝብን የማይዘልፉ አብራችሁ ከዚያ ወጣት ጋር ቅሬታችሁን ጠቅልላችሁ ባትጨምሩዋቸው እመርጣለሁ። በተለይ አበክሬ ለማስገንዘብ የምፈልገው፤ የአማራን እራሱን የመከላከል መብት ጠባብ ቡድን እያሉ የሚያጥላሉ "እኛስ ብለን ነበር" እያለ "ፖለቲካ ፈት" የሆነው "ጸረ አማራው" የኢያሱ ዓለማየሁ ፡ "ኒዮ-ካም" የኢሕአፓው ክፍል እንዲህ አይነቶቹ ክስተቶች ሲያዩ ሊጠቀሙበት ስለሚችሉ ያንን ለብተና ባሕሪያቸው ለመጠቀም ሊንደፋደፉ ስለሚችሉ ጀሮ አትስጡዋቸው)፡ እንዲህ ያሉ

ወጣቶች በቁጣ ሂደት በስሜት ስለሚጠቁ ‘የሚተፉት ቁጣ’ የምንጠብቀው ስለሆነ አሳሳቢ ቢሆንም በጊዜው እርማት እንዲደረግብት ወጣቶች ከዛ ዓይነት ስሜት እንዲርቁ መምከር ነው።

ካለፉት የግንጠላ አገር አፍራሽ “ኒዮ-ካም” ማርክሲስቶች ትምሕርት የራቁ ናቸው፤ የአገሪቷን አንድነት ይጠብቃሉ ብዩ ሳምነው የነበረ ወጣት ከሚባሉት አንዱ ይህ ወጣት ነው ብዩ ተስፋ ስጥልበት፤ ሰሞኑን ባወጣው “የፌስ ቡክ (?)ቪዲዮ” ዩ-ቱብ ላይ ተለጥፎ ያደመጥኩትን አፍራሽ ቁጣ እጅግ ቅር ብሎኛል። በዶ/ር ሙሉወርቅ ኪዳነማርያም <የግንጣላና “<የአስታጥቁን አታስጨርሱን>> ስብከት ቆስቓሽነት ምክንያት ሔኖክ የሺጥላ “የትግራይ ማሕበረሰብ የሚኖርብትን መሬት ከነሕዝቡ ጭምር፤ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ቢገነጠል ብዙም እንደማያሳስበው “በሚስት እና ውሽሚት” ምሳሌ እያስረዳ “Do we care! Go a head” ዓይነቱ፤ ትግሬዎች መገንጠል ከፈለጋችሁ ውትወታውን አብዝታችሁታል እና “ሂዱ” በማለት ለግንጣላቸው ውትወታ “አረንጓዴ መብራት” ከመፍቀዱ ባሻገር፤ ካለይ እንዳሳየሁት ንግግሩ ሙዝ እና ብርቱካን እያየ ያደገ ልጅ እና እባብ እያየ ያደገ ልጅ ፤ በምንም ዓይነት አንድ ዓይነት አስተሳሰብ ሊኖሮው አይችልም፡ (እኔም በትግሬነቴ ወላጆቼ እና ዘመዶቼ እንዲሁም ፋሮች፤ሶማሌዎች፤ወሎየዎች.... በዚህ ወጣት ጸያፍ ዘለፋ ተሰድበናል) ልጅ በባሕሪ ባሻገር የሚከተለውን ጸያፍ ዘለፋ በትግራይ ሕዝብ ላይ በመሰንዘር ወጣት የሺ ጥላ ትግሬውንም፤ዓፋሩን፤ሶማሌውንም፤ወሎየው ሕዝብ ሁሉ የትራምፕ አይነት ጸያፍ ዘለፋ ሰንዝሯል። በነገራችን ላይ ሔኖክም ሆናችሁ ሌሎቻችሁ ወያኔን ለማወቅ የተቸገራችሁ የምትመስሉ ስለ ግንጠላ አስምለክቶ አንድ ነገር ልነግራችሁ እፈልጋለሁ። ወያኔዎች የመገንጠል አጀንዳቸው ከመጀመሪያ ጀምሮ ሲሰሩበት እንደነበር ሁላችሁም ታውቃላችሁ የሚል እምነት አለኝ። ምን ማለት ነው? ኢትዮጵያን ለማፍረስ ማለት ነው። ያንን ለማሳካት ደግሞ አገሪቷ በ9 ክልሎች ከልለው፤ ለግንጠላ አመቻችተው ሰንደቃላማቸውን ሰጥተዋቸዋል። ግራኝ፤ሙሶሎኒ እና መለስ ዜናዊ የተጠቀሙበት ስልት አንድ እና ተመሳሳይ ነው። ሦስቱም የወል የሚባሉ እሴቶችን እና ታላላቅ ሰዎችን በማጥፋት ያተኮሩ ነበሩ (ናቸው)። ዛሬ ወያኔ እውን ለማድረግ እየጣለ ያለው ያንን ለማድረግ፤ በማገባደድ ላይ ነው። የመገንጠል ጠያቂው ክፍል የሚፈልገውን ምጣኔ ሓብት (እህል ጊተራዎች ሳይቀር) የተማረ ሃይልም ከማሳካቱ በላይ የታጠቀም ስለሆነ ያለ ፈቃድ የመገንጠል ችሎታ ያለው መሆኑን የታወቀ ቢሆንም፤ ለፖለቲካው

ምክንያት ያመቸው ዘንድ “ፈቃጆችን” በስሜት እንዲቆጡ በማድረግ ገፋፍቶ “እሺታን” የሚተባበሩ ክፍሎች መፍጠር ነበረበት እና ያለ ምንም ችግር እየፈጠረ ነው።

ታደግ ከሚባለው የሞረሹ አቶ ተክሌ የሻው መጽሐፍ የሊቁ ዮፍታሔ ንጉሴ ግጥም ልጥቀስ እና ልሻገር፤

<< አገሬ ተባብራ ካልረገጠች እርካብ
ነገራችን ሁሉ የእምቧይ ካብ፤የእምቧይ ካብ >>

ወጠቶቻችን በቁጣና ስሜት ተገፋፍተው ሆን ብለው በጥናት ወያኔዎችና ኤርትራኖች በሕረቡእም በግልጽም የሚቆሰቁሱትን የቁጣ ስሜት ዘመቻ፤ ‘ወጣቶቻችንም’ ያንን ስሜት በሌላ ተመሳሳይ አጸፋዊ ስሜት በመመለስ ያገራቸውን አንድነት እንዲፈርስ ሳያስቡት ወጥመዳቸው ውስጥ እየገቡላቸው ነው። ለዚህም ማሳያ ይኼወ የሰሞኑን የሔኖክ የሺ ጥላ ምላሽ በቂ ማሳያ ነው።

ብዙዎቹ እንደሚታውቁት፤ ወጣቱ ሔኖክ የሺ ጥላ ገጣሚና፤ለኢትዮጵያና ለአማራነቱ ነፃነት በመቆም የተለያዩ ክርክሮች እና ጽሑፎችን በሚዲያ የሚያሰራጭ ጎበዝ ወጣት ነው። በቅርቡ ቅር ብሎኛል። ደ/ር ሙሉወረቅ ኪ/ማርያም (ዛሬ ትግራይ ውስጥ ከወያኔዎች ይልቅ <<በአልትራ ፋሺዝም>> ትምህርት ብዙ ወጣቶችን የማስከተል አዝማሚያ እየታየበት ያለ ሊሂቅ ነው። ሙሉወርቅ ትግራይ ውስጥ የአንድ ዩኒቨርሲቲ ተቋም ዲን/አስተዳዳሪ/ የሆነ፤በርካታ መጽሐፍቶችን የጻፈ፤ ድሮ “የኢሕአፓ” ታጋይ የነበረ፤ ዛሬ ፖለቲካ ሳይንስ ምሁር፤ ታሪክ በምሳሌና በቀልድ ወግ ነጋሪነቱ እውቅና በማግኘት ወጣት ተከታዮችን በስፋት እያስከተለ የሄደ፤ ለትግራይ የበላይነትና ግንጠላ የቆመ ሙሉወርቅ፡= ሰሞኑን ስላስተላለፈው “ትግራይ መገንጠል አለባት፤ ወያኔ የትግራይን ሕዝብ አጋልጦ ለጠላቶቹ ሰጥቶታል፤ትግሬዎች እየተደፈሩ ነው፤ንብረታቸው ህይወታቸው አደጋ ላይ ወድቋል፤ ህወሓት ካልተከላከለለት ሕዝቡ ከአደጋ ለመከላከል ሲል እራሱን አስፈላጊውን የመከላከል ዝግጅት ማድረግ አለበት፤ በሻዕቢያ ላይ የጦርነት እርምጃ ይወሰድ፤ወጣት ተማሪዎች ከትግራይ ድምብር  ወደዚያ ያለው ለኛ አስጊ እየሆነ ስለመጣ ከድንበራችን መሻገር አንፈልግም እያሉ ስለሆነ፤ ኢትዮጵያ ማለት እኛ ነን፤ የእኛ ሕልውና ከሚጻረሩ ጋር መኖር ስላማንፈልግ ከዛ አደጋ እራሳችን ባስቸኳይ እናውጣ....” ሲል ያደረገው “ፋሺስታዊ” አደገኛ የብጥብጥ እና የግንጠላ ጥሪ፤ መሰረት ያደረገውን ጥሪ፡

‘ወጣት ሄኖክ የሺጥላ’ ያንን የሴራ (የተንኮል) ጥሪ ሰምቶ እንዲህ የሚል ምላሽ ሰጥቷል።

<< አትገንጠሉ፤ አትገንጠሉ ስንላችሁ የኢትዮጵያን ሕልውና የሚያከትመው፤የሚያጠፋው ይመስለን ስለነበረ በዚህ (እምነት) በእኛ እና በናንተ ያለው አመለካከት በፍጹም የተለየ ነው። ተው ከኛ ጋር ሁኑ፤ አትገንጠሉ ስንላችሁ የተረጎማችሁት ‘እኛ’ ከናንተ ከትግራይ ከሚባለው ምድር የተለየ ልዩ ጥቅም ስለምናገኝ መስላችሏል። ኖ! ምንም እንደማናገኝ እናንተም ታውቃላችሁ። ማስፈራሪያም ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ የዋህ በነበረበት ጊዜ ‘መገንጠል..... ስለሚመስላችሁ። ስለዚህ (ዛሬ) የትግራይ መገንጠል የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆድ ያባባል ብላቸሁ ከሆነ ተሳስታችኋል። የተፈጠሩበት ቦታ ድንጋይ ነው፡ ምንም ነገር የለውም፡ አትገንጠሉ ስንላቸው ሰውነታቸውን ፈልገን እንጂ ከምድራቸው ምንም ነገር የለም፡ ድንጋይ ነው።ውሽሚቱ ከሴትየይቱ ቤት መጥታ ታለቅሳለች፤እኔን እኔን ካልተቀበርኩ እያለች ስታለቅስ፤ ሚስትየይቱ በጣም ተናደድ *“እኔን እኔን ስትይ የሚደላው መስሎሻል፤ ግቢና ምክሪው ውስጥ ያነክትሻል”* አለቻት አሉ። በመሰረቱ እንደዚህ የከፉበት ምክንያት እኮ ምድራቸው ምንም ዓይነት ነገር ስለሌለው ነው። የ “ካራክተር” (ባሕሪ) መሰረት አድርጎ የሚገነባው ይህንን መሰረት አድርጎ ነው። ለም አካባቢ የሚኖር ሰው እና ደረቅ አካባቢ የሚኖር ሰው “ኤክስፒሪያንሱ” ይለያያል። ምድራዊ “ኤክስፒሪያንሱ”። ሙዝ እና ብርቱካን እያየ ያደገ ልጅ እና እባብ እያየ ያደገ ልጅ በምንም ዓይነት አንድ ዓይነት አስተሳሰብ ሊኖሮው አይችልም። ሰው ቤተሰቡን እና አካባቢውን ነው የሚመስለው። ስለዚህ ከኛ ጋር ሁኑ፤ሁኑ ስንላችሁ........።

እያለ የሰጠው ምላሽ የእነ ሙሉወረቅ የግንጠላ ሴራ ባጠመዱብን ወጥመድ እውን መሆን አለበት ብሎ ያለ ምንም ማንገራገር ከማጽደቁ አልፎ የትግራይ ሕዝብ፤የወሎ ሕዝብ፤ ዓፋር፤ሶማሌ ሕዝብ በነ ሔኖክ የምጣኔ ሐብት ይዘት የትርጉም ይዘት፤ ሙዝ እና ብርቱካን እያየ ያደገ ልጅ እና እባብ እያየ ያደገ ልጅ በምንም ዓይነት አንድ ዓይነት አስተሳሰብ ሊኖሮው አይችልም። ሲል እነዚህ የተጠቀሱ ማሕበረሰቦች ድንጋያማ፤አሸዋማ፤በረሃማ፤..ስለሆኑ ሙዝ እና ብርቱካን እየላጡ በምቾት እና በደስታ ካደጉ የነ ወጣት ሔኖክ የሺ ጥላ ማሕበረሰቦች ባስተሳሰብ የተለዩ ናቸው ሲል አስገራሚ የሆነ ትንተና አስተጋብቷል። ለመሆኑ ሙዝ እና ብረቱካን እየላጡ “እየተመገቡ” እያዩ

ደልቷቸው ያደጉ ልጆች እነማን ይሆኑ? ጎጃሞች፤ሸዋዎች፤ጎንደሬዎች'ወለየዎች ባጠቃላይ አማራዎች ናቸው? ለደርግ ዘመን ጀምሮ ወደ ኦሮሞ እና ሌሎች አካባቢዎች እየሄዱ በገዛ አገራቸው ብዙ ውርደት እያዩ ያሉት እናማን ናቸው?። አማራ አገር በርበሬ ካለ፤ትግሬዎች ጨው፤ወርቅ፤ጥራጥሬ፤ዕጣን፤የከርሰ መሬት መአድኖች ከሌሎቹ እጅግ የተከማቸ ንጥረ ነገር የያዘ ነው.. ሃብታም፤ለም የተባሉ አውራጃዎች አሉት፤ የደረቀ መሬት የተባለ አካባቢም በከፊል አሉ\\እንደ ሌሎቹ ክ/ሃገሮች......እነዚህ ትግራይ ውስጥ ካሉ፤ ጎጃም ቅቤ ካለ፤ ጋሞ ጎፋ ወይንም ጉራጌ ነጠላ ካለ ጠፍም ካንዱ ፍየል ከአፋሩም ከሌላም ሌላም ንግድ ልውጥ ካላደረገ ሙዝና ብርቱካን በማብቀሉ ብቻ ከሌሎች አካባቢዎች የሚፈልገው ነገር የለም ማለት አይደለም። የጥላሁን ገሰሰ “የምግብ  ይነቶች” የሚለው የጥላሁን ዘፈኖች ሔኖክ የሺጥላ አልሰማውም አልልም። ሁሉም ምን እና ከየት እየተፈላለገ=በመለዋወጥ ገበያ ለዘመናት እንደኖረ ጥላሁን ምስክር ነው።

ሙዝ እና ብርቱካን እየላጠ በቅምጥል ያደግን ልጆች ነን፤ እናንተ ደግሞ እባብ እያያችሁ ያደጋችሁ ድንጋይ መሬት ላይ ያደጋችሁ፤ የተለየ ባሕሪ ያላችሁ ሰዎች ናችሁ... እያለን ያለው ስለ አማራው ሃብታምነትን ቅምጥልነት እያወራ ከሆነ በማስረጃ የተደገፈ አይደለም።ለዛው ምክንያት ሲነግሩን ገበሬዎቹ “ጎጃም” ላይ ያለው መሬት በቂ እንዳልሆነ ነው የሚናገሩት፤ሸዋ የሚባለው በተለይ መንዝ የሚባለው ገደለማ እና አለታማ ጭራሽ ለግብርና የማይመች መሬት ነው። ወሎም እንደ ትግራዩ ግማሹ ምናልባት ለም ግማሹ ምድረ- በዳ ነው። ለዚህም ይሆናል የወሎ ርሃብ በከፍተኛ ጥቃት የተጋለጠው። ሁሉም አገራችን ነው። በሙዝና በብርቱካን ተቀማጥሎ ያደገ እባብ እያየ ያላደገ ኢትዮጵያዊ አለ ለማት ለኔ እጅግ አስገራሚ ነው። ከዚህ ሁሉ አፍራሽ ስሜት ወጥተው ወጣቶቻችን ከወያኔዎች ተሸለው እንዲገኙ እንጠብቃለን። ለመሆኑ እባብ ያልኖረበት ምድር እና ውቅያኖስ የት ይኖራል? እኔ ለምሳሌ ትግራይ ነው አደግኩት እንደ ወሎ “ዓይጥ” የሚርመጠመጥበት በጣም አሰቃቂ የሆኑ በየቤቱ ለጉድ የሚርመሰመሱ አይጦች ዓይነት መሬት ፍጹም አላየሁም፤ ታዲያ ይህ በወሎ ሕዝብ ላይ የባሕሪ ተጽእኖ አለው ሊለን ነው ወጣቱ ሔኖክ። ካለስ ምን ባሕር ይሆን? እባካችሁ በሕዝብ እንድነጋገር አትጎትቱን።

ለመሆኑ ሔኖክ የሺጥላ ወያዎች የትግራይን መገንጠል ሲያቀነቅኑ “ሂዱ እና ሞክሩት” ሲል ሶማሌዎች፤ኦሮሞዎች፤ዓፋሮች.....ስልጤዎች ....ከሔኖክ ጎሳ አብረው የሚኖሩ መሆናቸውና እኛም ሄደን እንሞክረው ቢሉት መልሱ “ሂዱና ሞክሩት” ሊላቸው ነው? እንደማይሉትስ  ዋስትናው ምንድ ነው? ለዚህ ለዚህ እማ ወላጆቻችን የተዋደቁላት መሬት “በቀላሉ” ሂዱና ሞክሩት የሚሉ ወጣቶች ማየት ከጀመርን፤ መለስ ዜናዊም እኮ እያለን የነበረው “አንቀጽ 39” ያጸደቅነው፤ እምቢ የሚል ካለ “ሂዱና ሞክሩት” ለማለት ነው ነበር ያለን። ታዲያ መለስ ዜናዊ የሰበከው አፍራሽ ቅስቀሳ “ትግሬዎች ብትገነጠሉ፤የትግራይ መገንጠል የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆድ ያባባል ብላቸሁ ከሆነ ተሳስታችኋል። የሚለን ሔኖክ ብምን ጥናት ያከናወነው ነው <<“የኢትዮጵያ ሕዝብ ከትግራይ ሐዘብ ጋር የተጋባውን ማሕበረሰብ ስታፈርሱ ቅር አይልንም ፤ስትፈልጉ ሂዱ ሆዳችን አይባባም”>> የሚል መሆኑን በራሱ መለኪያ ነው ወይስ ያከናወነው ጥናት አለ? አትገንጠሉ፤ አትገንጠሉ ስንላችሁ የኢትዮጵያን ሕልውና የሚያከትመው፤የሚያጠፋው ይመስለን ስለነበረ........ የምትለው አባባልህ አውነት ትግራይ ብትነጠል የኢትዮጵያን ሕልውና የሚያከትም፤ ሕልውናውን የሚያናጋው/የሚያጠፋው አይመስልህም? ሁሉም አንድ ባንድ እንዲህ ሲሄድ ኢትዮጵያ ብሎ ነገር ይኖራል ብለህ ትገምታለህ? ካልሆነ ለምን አያከትምም? ወጣቶች ከስሜት ውጡ! ከወያኔዎች፤ኢሕአፓዎች፤አነጎች እና አብነግ  ኒሂልስቶችና መሰል ብሐር ብሔረሰብ አቀንቃኝ “ኒዮ-ኮሚ ዎች”፡የተሻላችሁ እንድትሆኑ እንጠብቃለን።

አመሰግናለሁ ጌታቸው ረዳ  (ኢትዮ ሰማይ አዘጋጅ) getachre@aol.com